فضل الصيام


የጾም ትሩፋት



إعداد: الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም : ይሱፍ አሕመድ

http://t.me/alateriqilhaq



ምስጋና እስልምናን ከሐይማኖቶች ሁሉ የበላይ ለማድረግ በቅንና በትክክለኛው ጎዳና ላይ አድርጎ ሙሐመድን ለላከው ጌታ ለአላህ ይገባው። ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም፤ እንዲሁም ሙሐመድ የአላህ አገልጋይና መልክተኛ ናቸው ብየ በእርግጠኝነት እመሰክራለሁ። ሶላትና ሰላምታ ደግሞ በሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ሁሉ ይስፈን።

ከዚህ በመቀጠል፦

ጾም አላህን ከምንታዘዝባቸው ታላላቅ የአምልኮት ዘርፎች አንዱ ነው። ጾም ታላቅ የሚባዳ ዘርፍ መሆኑን እንዲሁም በጾም የሚገኘው ምንዳ የተነባበረ መሆኑን የሚገልጹ በርካታ ሐዲሶች መጠዋል።

የጾም ትሩፋቶች

አንደኛ፦ - ጾም አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - በሁሉም ማህበረሰብ ላይ ግዴታ ያደረገው የሚባዳ ዘርፍ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፦

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ كُتِبَ عَلَيْكُمُ الصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى الَّذِينَ مِن قَبْلِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ﴾

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም ከነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በእናንተም ላይ ተጻፈ ልትጠነቀቁ ይከጀላልና።" *(አል'በቀራህ፦ 183)*

ጾም በእርሷ ወደአላህ የሚቃረቡበትና ከፍተኛ ምንዳ የሚያገኙበት ታላቅ የሚባዳ ዘርፍ ባይሆን ኖሮ በሁሉም ማህበረሰብ ላይ ግዴታ አድርጎ ባልጻፈው ነበር። ከጾም ተስፋ የሚደረገው ሁሉንም ማህበረሰብ አደራ ያለበት የአላህ ፍራቻ ነው ።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፦

﴿وَلَقَدْ وَصَّيْنَا الَّذِينَ أُوتُواْ الْكِتَابَ مِن قَبْلِكُمْ وَإِيَّاكُمْ أَنِ اتَّقُواْ اللّهَ﴾

"እነዚያንም ከበፊታችሁ መጽሐፍን የተሰጡትን እናንተንም አላህን ፍሩ በማለት በእርግጥ አዘዝን።" *(አን'ኒሳእ፦ 131)*

ሁለተኛ፡ - ጾም በመጾም የሚገኘው ምንዳ በቁጥር ያልተገደበ ነው።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት አቡሁረይራ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

አላህ በሐዲሰል ቁድስ የሚከተለውን ተናግሯል፡ -

"ጾም ሲቀር የሰው ልጅ ስራ ሁሉ ለአርሱ ነው ፤ እንሆ አርሱ ለእኔ ነው ፤ እኔው እመነዳዋለሁ። ጾም ጋሻ ነው። በእንደኛችሁ የጾም ቀን ርካሽ ቃል አይናገር አይጩህ ፤ የሆነ ሰው በስድብ ቢሟገበዘው ወይም ቢጋደለው እንኳ "ጾመኛ ነኝ" ይበለው። የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ የጾመኛ የአፍ ጠረን ከአላህ ዘንድ ከሚስክ ሽታ ያማረ ነው። ለጾመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት ፤ ሲያፈጥር ይደሰታል ፤ ጌታውን ሲገናኝ ደግሞ በመጾሙ ይደሰታል።" *(ቡኻሪ፡ 1904, ሙስሊም፡ 1150)*

በሌላ የሙስሊም ዘገባ፡ -

"كل عمل ابن آدم يضاعف ، الحسنة عشر أمثالها إلى سبعمائة ضعف، قال الله عزوجل إلا الصوم فإنه لي وأنا أجزي به ، يدع شهوته وطعمه من أجلي"

"ጾም ሲቀር ፤ የሰው ልጅ አጠቃላይ ስራ ይነባበራል ፤ አንድ መልካም ስራ በአስር ቢጤዋ አስከ ሰባት መቶ ድረስ ትነባበራለች። እንሆ አርሱ (ጾም) ለእኔ ነው ፤ እኔው እመነዳዋለሁ ፤ ስሜቱን ምግቡን ለእኔ ሲል ነው የተወው።" በማለት አላህ ተናገረ። *(ሙስሊም፡ 1150)*

ይህ ታላቅ ሐዲስ የሚከተሉት ትሩፋቶች እንዳሉት ሸይኽ ሙሀመድ ብን ሷሊህ አል ' ዑሰይሚን - ረሂመሁሏህ - ይናገራሉ፡ -

1. አላህ ጾምን ከሌሎች ስራዎች መርጦ ለነፍሱ መለየቱ ጾም ከእርሱ ዘንድ ትልቅ ልቅና ስላለው፤ ስለሚወደው ፤ ከሌሎች ዒባዳዎች ይልቅ በጾም የዒባዳ ዘርፍ ኢኽላስ (ስራ ለአላህ ብቻ ተብሎ መሰራቱ) ይፋ ስለሚሆን ነው። ምክንያቱም ጾም በባሪያውና በጌታው መካከል ያለ ሚስጥር ነው። ከአላህ በቀር የሚያውቀው አንድም የለም። ጾመኛ ማንም ሳያየው ተደብቆ መብላት እየቻለ አላህን ፈርቶ ከምግብ ተከልክሎ ይውላል። ይህ የሚጠቁመው በድብቅ እንኳ ሊመለከተው የሚችል ጌታ እንዳለው ማረጋገጡ ነው። ከአላህ ዘንድ የሚገኘውን ምንዳ ተስፋ አድርጎ ቅጣቱን ደግሞ ፈርቶ ክልክል ነገሮችን ይተዋል። በዚህ ምክንያት ኢኽላሱን አላህ ያመሰግናል። ለዚህ ነው አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - ጾምን ከሌሎች ዒባዳዎች ለይቶ ወደነፍሱ ያስጠጋት።

አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - በሐዲሰል ቁድስ እንዲህ ብሏል፡-

"يدع شهوته وطعمه من أجلي"

"ስሜቱን ምግቡን ከእኔ ሲል ተወ።" (ሙስሊም፡ 1150)

የጾም ጥቅም ከሌሎች ዒባዳዎች የተለየ መሆኑ የትንሳኤ ቀን ይፋ ይሆናል።

ሱፍያን ብን ኡየይና - ረሂመሁሏህ - የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - የትንሳኤ ቀን ጾም ሲቀር በባሮች ላይ ያለባቸውን በደል በሌሎች መልካም ስራዎች ያካክሳል። ሌሎችን በደሎች ሐላፊነቱን እርሱው ይሸከማል። በጾሙ አማካኝነት ጀነት ያስገባዋል።" (አል'በይሓቂይ ፊ"ሱነን አልኩብራ፡ 4/274)

2. አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - ጾምን አስመልክቶ "እኔው እመነዳዋለሁ" በማለት ተናገረ። የሚሰጠውን ምንዳ ወደተከበረው ነፍሱ አስጠጋ። ምክንያቱም መልካም ስራዎች ምንዳቸው ይነባበራል። አንድ መልካም በአስር ቢጤዋ እስከ ሰባት መቶ ከዚያም በላይ ይነባበራል። የጾም ምንዳ ግን ቁጥሩ ሳይገለጽ አላህ ወደነፍሱ ነው ያስጠጋው። አላህ የለጋሾች ሁሉ ለጋሽ ፤ የሰጭዎች ሁሉ ሰጭ ነው። የጾመኛ ምንዳ ያለምንም ግምት ታላቅ ሆነ። ምክንያቱም ጾም በውስጧ ሶስቱን የትዕግስት አይነት አቅፋ ይዛለች። አላህን በመታዘዝ መታገስ ፤ ወንጀል ከመስራት መታገስ ፤ በአላህ ውሳኔ ማለትም ሲርበው፣ ሲጠማው፣ በአካሉ ላይ ድካም ሲሰማው መታገስ ናቸው። በዚህም ጾመኛ የሆነ ሰው ከትዕግስተኞች መሆኑ ተረጋገጠ ማለት ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿إِنَّمَا يُوَفَّى الصَّابِرُونَ أَجْرَهُم بِغَيْرِ حِسَابٍ﴾

"ታጋሾቹ ምንዳቸውን የሚሰጡት ያለግምት ነው።" (አዝ ዙመር፡ 10)

3. ጾም ጋሻ ነው። ጾም በመጾም ከዛዛታ ወሬዎች ፣ ከጸያፍ ተግባራቶች መጥጠበቅ ይቻላል። ይህን አስመልክቶ የአላህ መልክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"በአንዳችሁ የጾም ቀን ርካሽ ቃል አንደይናገር አንደይጮህ" ብለዋል። (ቡኻሪ፡ 1904, ሙስሊም፡ 1150)

ጾም ከእሳት ይጠብቃል።

أخرج الإمام أحمد في مسنده عن جابر بن عبد الله رضي الله عنه أن النبي صلى الله عليه وسلم قال: "الصيام جنة يستجن بها العبد من النار"

ኢማም አህመድ በዘገቡት ጃቢር ብን ዓብዲላህ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡ -

"ጸም ባሪያው አሳትን የሚከላከልበት ጋሻው ነው፡" *(አህመድ፡ 14669, ሀዲሱን አልባኒ ሀሰን ብለውታል "ሶሂህ አት' ተርጊብ ወተርሂብ፡ 981)*

4. የጾመኛ የአፉ ሽታ ከአላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - ዘንድ ከሚስክ ያማረ ሽታ አለው። ምክንያቱም የጾሙ ውጤት በመሆኗ ከአላህ ዘንድ መልካምና ተወዳጅ ሆነች ። ይህ የሚጠቁመው ከአላህ ዘንድ ጾም ትልቅ ደረጃ ያለው መሆኑን ነው። አላህን ከመታዘዝ የመነጨ በመሆኑ ከሰዎች ዘንድ መጥፎ ጠረን ቢሆን እንኳ ከአላህ ዘንድ ተወዳጅ ይሆናል ማለት ነው።

5. ለጾመኛ ሁለት ደስታዎች አሉት። አንደኛው በሚያፈጥር ጊዜ ይደሰታል ፤ ሁለተኛው ደግሞ ጌታውን በሚገናኝ ጊዜ ይደሰታል። ሲያፈጥር መደሰቱ ከዒባዳዎች ሁሉ ትልቅ የሆነውን ጾም አቅም ሰጥት በሰላም በማጠናቀቁና በዚህም ጸጋውን ስለዋለለት ይደሰታል ማለት ነው። አላህ ያዘዛቸውን ጾም የማይጾሙ ፤ በጾም ጊዜ የሚበሉ የሚጠጡ ፤ ከሚስቶቻቸው ጋር የሚገናኙ ስንት ሰዎች አሉ?! ከጌታው ጋር ሲገናኝ የሙእሚን ደስታ ደግሞ አስፈላጊ በሆነበት ወቅት ማለትም ጾመኞች የታሉ? ጾመኞች እንጅ ማንም በማይገባበት ረያን በሚባለው በር ግቡ እየተባሉ በሚጠሩበት ወቅት የጾሙን ምንዳ የተሟላና የተነባበረ ሆኖ ሲያገኘው በጣም ይደሰታል።

ሶስተኛ፡ - የትንሳኤ ቀን ለእርሱ ሸፈዓ ይሆነዋል።

ኢማም አህመድ ፣ ጦበራኒና ሀኪም በዘገቡት ዓብደላ ብን ዓምር ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፏል፡ -

"ጾምና ቁርአን የትንሳኤ ቀን ለባሪያው ያማልዳሉ። ጾም "ጌታየ ሆይ! በቀን ከምግብ፣ ከመጠጥ እና ከስሜት ከለከልኩት ፤ ስለርሱ ሸምግልናየን አባክህ ተቀበለኝ።" ይላል። ቁርአን ደግሞ "በሌሊት እንቅልፍን ከለከልኩት ፤ ምክጀየን አባክህ ተቀበለኝ" በማለት ያማልዳሉ።" *(አህመድ፡ 6626, ሙስተድረክ ሀኪም፡ 1/740, ሀዲሱን አልባኒ ሀሰን ብለውታል "ሶሂህ አት' ተርጊብ ወተርሂብ፡ 984)*

አራተኛ፡ - በጀነት ጾመኞች እንጅ ማንም የማይገባበት ረያን የሚባል በር አለ።

ቡኻሪ እና ሙስሊም በዘገቡት ሰህል ብን ሰዕድ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፏል፡ -

“በጀነት ረያን በመባል የሚጠራ በር አለ። ጾመኞች ብቻ የቂያማ ቀን ይገቡበታል። “ከእነርሱ ውጭ ማንም አይገባበትም።” ይባላል። “ጾመኞች የታሉ” ይባላል፤ እነርሱም ይቆማሉ፤ ከእነርሱ ውጭ ማንም አይገባም፤ የገቡ ጊዜ ይዘጋል ፤ አንድም በእርሱ አይገባም።” *(ቡኻሪ፡ 1896, ሙስሊም፡ 1152)*

አምስተኛ፡- አንድ የአላህ ባሪያ ሸሪዓው ባዘዘው መሰረት በኢኽላስና ረሡልን ﷺ በመከተል ኢስላማዊ ተግባራትን ከፈጸመ የሚሰራቸው ስራዎች ሁሉ ፍሬ ያፈራሉ። በሐቅ ላይ ይጸናል ፤ ኢማን ይጨምራል ፤ እርግጠኛነቱ ይጠነክራል፤ ባማረ ስነ-ምግባር ይዋባል ፤ ስሜቱን ይሰብራል ፤ አላህን ብቻ ይፈራል ፤ እርሱን ብቻ ተስፋ ያደርጋል።

ኢብን አልቀይም - ረሂመሁሏህ - የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

“የጾም ጥቅሞች በሰላማዊ አቅልና ትክክለኛ በሆነ ተፈጥሮ የተረጋገጡ በመሆናቸው አላህ ለባሮቹ እዝነት ፣ መልካም ስራና ከእሳት መከላከያ ጋሻ አድርጎ ለባሮቹ ደንግጎታል።” *(ዛዱል መዓድ፡ 2/28)*

አላህ ሆይ! ያላወቅነውን አስተምረን ፤ ባሳወከን ጥቀመን ፤ አንተ በምትፈልገው አይነት ጾምን ተፈጻሚ ከሚያደርጉ ሰዎች አድርገን።

وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وصحبه وسلم

فضل الصيام

የጾም ትሩፋት

إعداد: الشيخ عبدالرزاق بن عبدالمحسن البدر

ትርጉም : ይሱፍ አሕመድ



ባህር ዳር በሚገኙ የአህለሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሐደራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ኪንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alateriqilhaq